## <u>የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ትረስት ፈንድ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ይፋ ሆነ።</u>

በቅርቡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐብይ አህመድ በተለያዩ ሃገራት የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የተሻለች ኢትዮጵያን ለመገንባት በሚደረገው ጥረት የበኩላቸው እንዲወጡ ጥሪ ማቅረባቸው ይታወሳል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በወቅቱ በውጭ ሃገራት የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በየቀኑ ቢያንስ አንድ ዶላር ወደ ኢትዮጵያ በመላክ ለተለያዩ የልማት ስራዎች ድጋፍ እንዲያደርጉ ጠይቀው ነበር። በዚህም በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን ተሳትፎ ለማቀናጀትና የልገሳውን ገንዘብ ለማሰባሰብ፥ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ትረስት ፈንድ በሚል ስም ሂሳብ ተከፍቷል። የሂሳብ ቁጥሩም **1000255726725** ነው። ገንዘቡን ለማስገባትም በቅርቡ ድረ ገጽ የሚከፈት ሲሆን እሱን በመጠቀም፥ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ስዊፍት አድራሻ እና **CBETETAA** በመጠቀምና ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዓለም አቀፍ ገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶችን በመጠቀም ይሆናል። ገንዘብ አስተላላፊዎቹ **ዌስተርን ዩኒየን፣ ኤክስፕረስ መኒ፣ ቦሌ አትላንቲክ ኢንተርናሽናል፣ መኒ ግራም፣ ዳሃብሽል መኒ ትራንስፈር፣ አል አንሳሪ (ካሽ ኤክስፕረስ)፣ ወርልድ ሬሚት፣ ትራንስፋስት መኒ፣ ካህ ኤክስፕረስ መኒ ትራንስፈር፣ ጎልደን መኒ ትራንስፈር፤ ላሪ ኤክስቸንጅ፣ ተወከል መኒ፣ ዜንጅ ኤክስቸንጅ፣ ፓኮ መኒ፣ ኢርማን ኤክስፕረስ፣ ባካል መኒ ትራንስፈር፣ ዲቫይን (ብሉ ናይል)፣ ዳዊት መኒ ትራንስፈር፣ ቲ እና ዋይ ሬሚት እንዲሁም አስጎሪ መኒ ኤክስፐረስን** በመጠቀም ይሆናል ነው የተባለው። ሃምሌ 11 ፣ 2010 (ኤፍ ቢ ሲ)




የፌዴራል የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽህፈት ቤት
The FDRE Government Communication Affairs Office